**ኢ.ኤ.ስ.ቲ.ኤ. ማን ነው?**

ኢ.ኤ.ስ.ቲ.ኤ. ዘወትር ለሃያ አራት ሰዐት አገልግሎት የሚሰጥ፣ ከ550 ሰራተኞች በላይ የሚስተዳደርና ለአምስት ሚልዮን የቪክቶሪያ ነዋሪዎች የሚያገለግል ድርጅት ነው። ድርጅቱ 000 የስልክ አገልግሎት እና ከዚህ በታች የተዘረዘሩት አገልግሎት ያጠቃልላል።

- ቪክቶርያ ፖሊስ (ሜልበርን ከተማ እና ግረተር ጂሎናግ አከባቢ)
- አምቡላንስ ቪክቶርያ (ሜልበርን ከተማ)
- የከተማ እሳት አደጋ ቢርገድ (የከተማ እሳት ወረዳ)
  የአገር እሳት አደጋ ባለስልጣን (አገር አቀፍ)
- የቪክቶርያ ድንገተኛ አገልግሎት (አገር አቀፍ)

**የድንገተኛ እርዳታ ከፈለግህ 000 ደውል**

000 የሚደወለው በሂወት አስፈሪ ወይም ግዜ የማይሰጥ ሁኔታ፥ የፖሊስ፣ የእሳት ወይም የአምቡላንስ እርዳታ ሲፈለግ ብቻ ነው።

አንዳንድ የድንገተኛ ምሳሌዎች እንደሚከተሉ ናቸው፥

- የአየር የባቡር ወይም የውሃ ሙላት አደጋ
- መተንፈስ የሚከለክል አለርጂ
- መድማት (ከባድ)
- መተንፈስ አለመቻል(ለምሳሌ ከባድ አዝማ)
- የስኳር በሽታ (አእምሮ መሳት/ መደናገር / ለየት ያለ ሁነታ ማሳየት)
- ከልክ በላይ አደገኛ ዕጽ መውሰድ
- መስመጥ
- የኤለትሪክ አደጋ/ ቃጠሎ / የኢንዱስትሪ አደጋ
- የፈንጅ ወይም ቦምብ አደጋ
- ለሂወት ወይም ንብረት የሚያስፈራ ኣሳት
- የልብ ድካም (ተጠርጣሪ)
- የመንገድ አደጋ
- የጨጓራ ቁርጠት(ሃይለኛ)
- ምት (ተጠርጣሪ)
- ወጥመድ የተያዘ ሰው
- ስቃይ(ቊስል)
- ልብ ያጠፋ ሰው
- ህውከት (ጥቃታ /በደል/ የቤት ውስጥ)

አስታውስ፡-ድንገትኛ መሆኑና አለመሆኑ እርግጠኛ ካልሆንክ 000 ደውል፡ ስልክ አንሺዎቹ ይረዱሃል።

**000 ስትደውል ማስታወስ ያለብህ ነገሮች፡-**

- ረጋ በል
- በገሀድ ድንገቱ የት እንደሆነ ተናገር
- በገሀድ ድንገቱ ምን እንደሆነ ተናገር
- በተቻለህ መጠን ስልክ ተቀባዮቹ የጠየቊህን ጥዬቄዎች በደንብ መልስ
- ስልክ አንሺዎቹ ስልኩን እንድትዘጋ እስከሚነግሩህ ድረስ ስልኩን አትዝጋ
- ለራስህ እና ለሌሎች ጉዳት መድረስ ከሚችሉ ነገሮች ጠንቀቅ በል (ለምሳሌ፡ ከአደጋ በኋላ የወደቀ የኤለትሪክ መስመር፡ ጥለኛ፣ የእሳት ነጣሪ)